ሙሐመዲዩ ለልጆች

(አንደኛ ደረጃ

አሏህን ማወቅ)



www.youth-mission.com

Tawheed for children

ተውሂድ ለልጆች

አሏህን ማወቅ

All right reserved

© የወጣቱ ተልዕኮ
የወጣቱ ተልዕኮ የኦንላይን እትም 2010
ሰሜን ወሎ ወልድያ

ahmedyesuf29@gmail.com
+251927790323
https://youth-mission.com



የወጣቱ ተልዕኮ

Presented by: Youth-Mission
Online Amharic Islamic
Books Publishing.


بسم الله الرحمن الرحيم

بسم الله الرحمن الرحيم

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

ምዕራፍ 1

ልጆች አሏህ ማን ነው?

አሏህ አረብ(ጌታ) ነው።

አሏህ የማንኛውም ነገር ፈጣሪ ፣ ሰጭ ፣ ነሽ ሲሆን አምልኮት ለእሱ ብቻ የሚገባ፣ እሱም ውብና ሙሉ የሆኑ ስምና ባህርያቶች ያሉት ጌታ ነው።



ከአሏህ ውጭ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የሌለ መሆኑን እና ሙሐመድ የአሏህ እውነተኛ ባሪያና መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ። ልጆች ይህ አባባል ወይም አረፍተነገር ሸሃዳ ተብሎ ይጠራል። ሸሃዳ ማለት የምስክርነት ቃል ማለት ነው።

አሏህ ጌታ ነው

ልጆች አሏህ በዙርያችን የምናያቸው እና የማናያቸው ፍጥረቶች ጌታ ነው። ለምሳሌ የመላኢካዎች ፣ የጅኖች ፣ የሰዎች ፈጣሪ ነው። አሏህ መላኢካዎችን ከብርሃን የፈጠረ፤ ጅኖችን ከዕሳት የፈጠረ ጌታ ነው።

ልጆች ሁሉም መላኢካዎች አሏህን ይገዛሉ፤ ለእሱም ይሰግዳሉ። አልታዘዝም አይሉም ሁሌም ታዛገሮች ናቸው። ነገርግን ከጅኒዎች በአሏህ የሚያምኑ ሙስሊሞች አሉ። ከጅኒዎችም አሏህን የማይገዙ ፣ አሏህን የማይታዘዙ ፣ በእሱም የማያምኑ ፣ መጥፎ ነገሮችን የሚሰሩ ፣ ሰዎችን ወደ መጥፎ ነገሮች የሚጣሩ አሉ። ታዲያ የነዚህ መሪ የሆነው ሸይጧን ነው።

አሏህ እኔን ፈጥሮኛል፤ አሏህ አንተንም ፣ አንችንም ፈጥሯችኋል። እናም አሏህ መላኢካዎችን እና ጅኖችን ፈጥሯቸዋል።

አላህ ለእኛ ብዙ ነገሮችን ሰጥቶናል። ለሁሉም ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ሰጥቷቸዋል። አላህ ለእኛ ህይወት ሰጥቶናል፤ መልሶም ይወስዳታል። አላህ እምናይበት አይን ፣ እምንተነፍሰውን አየር ሰጥቶናል። አላህ እኛን በህይወት እንደሚያኖረን ሁሉ ሌሎች ሰዎችንም በህይወት እንዲኖሩና እንዲሞቱ የሚያደርጋቸው እሱ አላህ ነው። ከላይ ያነበባችኋቸው ነገሮች በሙሉ የሚያመላክቱት ተውሂደ ሩቡብያ(አላህ በጌታነቱ አንድ ብቻ) መሆኑን ነው።



ጥያቄ

ልጆች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሞክሩና ትክክል መሆናችሁን አረጋግጡ።

1 ጌታህ ማነው?

2 ህይወት የሰጠህና በህይወት ለመኖር የሚረዳህን ነገር ያስገኘህ ማነው?

3 የፈጠረህ ማነው?

4 ህይወትህን የሚወስዳት ማን ነው?

ማጠቃለያ

እነዚህን ጥያቄዎች በትክል ከመለሳችሁ የአሏህን ጌታነት ተረድታችኋል ማለት ነው።

ልጆች ተውሂደ ሩቡብያ ማለት ብቸኛውና እውነተኛው ጌታ አሏህ ብቻ ነው ማለት ነው።

አሏህ የማንኛውም ነገር ፈጣሪ ሲሆን ሁሉም ነገር ለአሏህ ነው። ተውሂድ ማለት ምን ማለት ነው? ተውሂድ ማለት አሏህን አንድ ማድረግ ወይም አንድና ብቸኛ መሆኑን ማረጋገጥ ማለት ነው።

ተውሂደ ሩቡብያ ማለት አሏህን በጌታነቱ አንድ ማድረግ ማለት ነው። በሌላ አገላለፅ ጌታነት ለአሏህ ብቻ የሚገባ መሆኑን ማረጋገጥ ማለት ነው።



ምዕራፍ ሁለት

ልጆች አላህ ሐሊቅ(ፈጣሪ) ነው። ሁሉንም ነገር የፈጠረው እርሱ ነው። ሰማያትን እና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው ያሉ ነገሮችን ሁሉ የፈጠረው እሱ አላህ ነው። ሰባት ሰማያትን እና ሰባት ምድርን ፈጥሯል። ከሰባት ሰማዮች ውስጥ አንዱን እንጅ ሌሎችን አናያቸውም። ምክኒያቱም ሌሎቹ ያሉት እኛ ከምናየው ሰማይ በላይ ናቸውና። ከሰባቱ ምድሮችም እኛ ያለንበትን እንጅ ሌሎችን አናያቸውም።



አላህ እኛ የምንተኛበትን ጊዜ ሌሊትን ፈጥሯል። የቀን ብርሃንንም ፈጥሯል። ፀሀይን ፣ ጨረቃን ፣ ከዋክብቶችን ውብ አድርጎ ፈጥሯቸዋል። ማን?.....አላህ ተራራዎችን ፣ ኮረብታዎችን ፣ ባህሮችን ፣ ውቅያኖሶችን ፣ እንስሳቶችን ፣ ዛፎችን ፈጥሯል።

ልጆች ብርቱካን ፣ ሙዝ ፣ አበባ ትወዳላችሁ አይደል ታዲያ ብርቱካንን የፈጠረው ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ሙዝንስ የፈጠረው ማነው? አበባዎችን የፈጠረው ማነው? አሏህ የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው ካላችሁ በትክክል መልሳችኋል።



ጥያቄ

ልጆች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሞክሩና ትክክል መሆናችሁን አረጋግጡ።


1. የማንኛውም ነገር ፈጣሪ ማነው?
2. ፀሀይን እና ጨረቃን የፈጠረው ማነው?
3. ሰማዬችን እና ምድሮችን የፈጠረው ማነው?
4. ተራራዎችንስ የፈጠረው ማነው?
5. ልክ እንደ ዝሆን ፣ ጥንቸል ፣ ጦጣ ፣ ግመል ፣ ወፍ እና ልክ እንደ ላም ያሉ እንስሳቶችን የፈጠረ ማነው?





ልጆች ፀሀይን ባያችሁ ጊዜ ማን እንደፈጠራት አስቡ። ፀሀይ ሙቀት ትሰጠናለች። ምድር ላይ ያሉ ብዙ ነገሮች የፀሀይን ሙቀት ይፈልጋሉ። ሙቀቷንም ብርሃኗንም እንፈልጋለን።

ጨረቃ ሙሉ ሆና ባያችሁ ጊዜ ምን ያህል ቆንጆ እንደሆነች አስቡት። ጨረቃ የሯሷ መንገድ አላት፤ ፀሀይም የራሷ መንገድ አላት።



ከአሏህ ድንቅ ፍጥረቶች እነዚህ የምትመለከቷቸው ትልልቅ ተራራዎች ፣ ውቅያኖሶች ፣ ደመናው ፣ ዝናቡ ፣ የፏፏቴ ውሃ ፣ አበባዎች ፣ የአትክልት ቦታዎች ፣ በረሃው ፣ ባህሩ ፣ ጨረቃው ፣ ፀሀዩ እንዴት ያሉ የሚያስገርሙ የሚያማምሩና የሚያስደስቱ ፍጥረቶች እንደሆኑ ተመለከታችሁ? ጎበዝ ልጆች! ታዲያ የእነዚህ ሁሉ ፈጣሪ አሏህ ነው።

ልጆች አሏህ ይፈጥራልም ያስገኛልም። አሏህ ሐሊቅ(ፈጣሪ) እና ረዛቅ(ሰጭ) ነው። ከሰማይ የሚወርድ ዝናብ ይሰጠናል። የምንበላውን ምግብና መጠጥ ይሰጠናል። የምንሰማባቸውን ጆሮዎች ፣ የምናይባቸውን አይኖች ፣ የምንተነፍስበትን አየር እና ገንዘብ ሰጥቶናል።






ይህን ሁሉ ስላደረገልንም እናመሰግነዋለን እንወደዋለንም። እንወደዋለን ምክኒያቱም ፈጥሮናል፤ ብዙ ነገሮችንም ሰጥቶናል። እንወደዋለን ምክኒያቱም መስሊሞች አድርጎናል።

ልጆች አሏህን እንወደዋለን! ስለዚህ ያዘዘንን ነገር እንሰራለን። እንድንከለከል ከነገረንም ነገር እንርቃለን። እሱንም ብቻ እንለምናለን። ይህ የአምልኮት ትርጉም ሲሆን ተውሂደል ኡሉህያ የአምልኮተ አሏህ አንድነት ተብሎ ይጠራል። በሌላ አገላለፅ አምልኮት የሚገባው አንድ አሏህ ብቻ እንደሆነ ማረጋገጥና ማመን ማለት ነው።

ልጆች አሏህን እንወደዋለን ምክኒያቱም አሏህ እጅግ በጣም አዛኝ ፣ ፍትሃዊ ነው። እንወደዋለን ምክኒያቱም ቆንጆ ስሞች አሉትና። እሱ ሁሉን ተመልካች፤ ሁሉን የሚያይ ነው። እንዲሁም እሱ ሁሉን ሰሚ ነው፤ ሁሉንም ነገር ይሰማል። ታዲያ እሱ ከሁሉም ነገር በላይ ከሆነ ከሰማይ ከዙፋኑ ላይ ነው ያለው። ሁሉንም ነገር ያውቃል። ውብ ፊት አለው ነገርግን እርሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም። ይህ የስምና ባህሪያቶች ተውሂድ ነው።



ጥያቄ

ልጆች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሞክሩና ትክክል መሆናችሁን አረጋግጡ።

1. አላህን የምንወደው ለምንድነው?

2. ሙስሊም ያደረገን ማነው?

3. ልንታዘዘውና በብቸኝነት ልንገዛው የሚገባ ማነው?

አላህን ብቻ ነው የምንገዛው፤ አላህንም ብቻ ነው የምንለምነው።



ሶላት ስንሰግድ ግንባራችነን እና አፍንጫችነን መሬት ላይ እንደፋለን አይደል ልጆች? አዎ! ይህ ሱጁድ ተብሎ ይጠራል። ሱጁድ የምናደርገው ለአላህ ብቻ ነው።

ልጆች አላህን እንታዘዘዋለን፤ አናምፀውም። ምክኒያቱም አላህ ስንታዘዘው ይወደናል። ስናምፀው አይወድልንም። ስንታዘዘው ብዙ ነገሮችን ካለን ነገር ላይ ጨምሮ ይሰጠናል። ሳንታዘዘው ስንቀር ግን ሊቀጣን ይችላል። ወይም ደግሞ እንዲምረን ከጠየቅነው ይምረናል። ምክኒያቱም መማር ይወድል።



እኛ የኢስላም ልጆች አሏህን እንወዳለን።

ነብያቶችን እና መልዕክትኞችን እንወዳለን።

የአማኞች እናት የሆኑትን የነብዩን ሚስቶች እንወዳለን።

ሁሉንም ሶሃቦች እንወዳለን።

አሏህ በእስልምና ላይ እንዲያሳድገን ፣

እሱ እንድንኖር እንደሚፈልገው እንዲያኖረን ፣

ሙስሊሞች ሆነን እነድንሞት እና የጀነት እንዲያደርገን፣

የእሱን ፊት ከሚያዩት እንዲያደርገን እንለምነዋለን።

አሚን!

የተከበራችሁና የተወደዳችሁ ውድ ሙስሊም አባቶች ፣ እናቶች ፣ ወንድሞች እና እህቶች እንደ ምታውቁት ልጆች የነገ ትውልድ የኢስላም ተረካቢዎች ናቸውና ልጆቻችነን ወይም ታናሾቻችነን በኢማን ፣ በእውቀት ፣ በሐያዕ ፣ በትቅዋ እና በመለካም ባህሪያት ኮትኩተን ልናሳድጋቸው ይገባል። ይህም በእያንዳንዳችን ላይ የተጣለ ግዴታ ነው።

ታዲያ ይህን ለማድረግ ገና በለጋ እድሚያቸው የተለያዩ መፅሐፎችን እያነበብን ወይም ደግሞ ገዝተን በመስጠት ስለ ኢስላም እንዲያጠኑ ማድረግ እውቀት እንዲጨብጡ ማድረግ ይኖርብናል። ይችንም አንስ ያለች ተውሂድ ለልጆች የምትል ፅሁፍ ለልጆችዎ ፣ ለታናሽዎ ቁጭ ሲሉ በማስነበብም ይሁን በማስደመጥ ልጆቻችን በትክክለኛ አቂዳ ላይ ተኮይኩተው እንዲያድጉ እንሞክር።

ወሰላሙ አለይኩም ወረህመቱሏሂ ወበረካቱህ!

ማንኛውም አይነት ሃሳብ አስተያየት ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ +251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት https://youth-mission.com ይጎብኙና መልዕክት ያስቀምጡልን። ጀዛኩሙላህ ኸይረን ከሲረን!


رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا إِنَّكَ
أَنْتَ السَّمِيعُ العَلِيمُ